# የኢትዮጵያ ህዝብ ትግልና የሃይሎች አሰላለፍ

ብዙ ተብሏል፡ ብዙ ተነግሯል፡ እጅግ ብዙ በጣም ብዙ ታይቷል። ተደጋጋሚ ምርጫዎችንም አልፈናል።

በነዚህም ምርጫዎችና የፖለቲካው ሂደት ዙሪያ ተስፋ የመቁረጥ ከንፈር የመንከስ፡ የድርጅቶችን መከፋፈል አይተናል፡ አሁንም አለቀመም። እንደገና አፍራሾች በፊናቸው አዲስ ድርጅት ፈጣሪዎች ሁነው አለን ሲሉ፡ ሀቀኞ ሲወገዙ፡ ካህዲዎች ሲወደሱ፡ ጠባብ ብሄርተኞች ሲታቀፉ፡ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊነት አክራሪና ጠብ አጫሪ; በጥላቻና በተራ በቂም የሚነዳ ሺፍታ፡ እንደሆኑ ተደርገው ጥላሸት ሲቀቡ በተደጋጋሚ ማየታችን መስማታችን ለገሚሶቻችን ቢያደነዝዘንም እውነታውን እንዳናይ ቢሸፍነንም፡ የጠላታችን የተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ትግራይ በህዝባችን ላይ ያሰፈነውን ፋሽስታዊ አገዛዝና ኢትዮጵያን ለመብታተንና አገር እንዳይኖረን ለማድረግ የተያያዘውን ዘመቻ ምንጊዜም ቢሆን ልናመልጠው የማንችለው ሃቅ ስለሆነ አሁንም ቢሆንም በየፊናችን መንጫጫታችንን አላቆንም።

ለብዙዎቻችን ያለፈው የ18 አመት ትግል መና የቀረና ውጤት አልባ አርገን እናየዋለን። እርግጥ ህዝቡ የስልጣኑ ባለቤት ካለመሆን አንፃር፡ በላዩ ላይ የተጫነውን የጨለማ ኑሮ ለማንሳት ካለመቻሉና ነፃነት ካለማግኘቱ አኩያ ከተመዘን እርግጥ የተባልው አባባል እውነት ሊመስል ይችላል። ይህ አይነት አስተሳሰብ ጠላት የሌለውን ሃይል እንዳለው ከማስመሰሉ በላይ፡ የትግሉን ሂደትና ውስብስብነት አለመረዳት ነው። የትግሉ ውጤቱ ነገ ተነገ በስቲያ ይታፈሳል ብለን እንደ እርሻ ምርት ጊዜውን ጠብቀን የምናጭደውና ምርቱን በሆይታ ጭነን ወደ ጎተራ የምንከተው አይነት ሆኖም አያውቅም።

ስለሆነም በኢትዮጵያዊነትና በጠባብ ብሄርተኝነት መካከል ያለው ትግል ሲብሰለሰል ኖሮ በ97ቱ ምርጫ ወቅት ካሳየው ነገር ቢኖር አንድ ሀቅ ብቻ ነው።ይህም ጠባብ ብሄርተኛነት በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተጠላ ብቻ ሳይሆን ህዝባችን እንደጠላት አይቶት አይመቱ ምት መቶ ወያኔን ተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ትግራይ ያሽመደመደው። ይህ ድል ምጊዜም ቢሆን የማይፋቅ ጠባብ ብሄርተኛነት ተመልሶ በሰላም ሊገዛ የማይችልበትን ሁኔታ አስረግጦ አልፏል። ይህን ድል ለማሳነስና ዝቅ አርጎ ለማየት የሚሞክሩ ሁሉ ትግሉን አለምርዳት ይሆናል።

ጠባብ ብሄርተኛነት በዚህ ሁኔታ ሲመታ እንደ ማንኛውም የጨቁኝ ስርአትና አገዛዝ የአልሞት በይ ተጋዳይነት ግብግቡን መቀጠሉ የማይቀር ነው። እድሜውን ለማራዘም አዳዲስ ወዳጆችን በተለያየ መንገድ ለመፍጠር ይሞክራል፡ ስውር የሰለባ መንገዶችን ያበጃል፡ በመጨረሻም ችንፈቱን ለመሸፈንና አሁንም መርዙን ለመዝራት ሲል ኢትዮጵያነትን ከኔ በላይ ማን ነው የሚወድ ይላል።

ይህ የምናውቀው ሃቅ ነው። ታዲያ ይህ ግልፅ ሆኖ ከሆነ ድንቅ ነውና የዛሬውን ምርጫ የአሰተሳሰብ ይዘትና የሃይል አሰላለፍ መሰረታዊ ከሆነ የንድፈ ሀሳብ አንፃር አበጥሮ ማቅረብ በአሁኑ ስዐት አንገብጋቢና ወቅታዊ ነው።

በዚህ ሸር ጉድ በሚባልለት ምርጫ ውስጥ የሚሳተፉትም የማይሳተፉትም አንድ ተመሳሳይ ባህሪ እናይባቸዋለን፡ ሁለቱም ወገኖች ወያኔን ያወግዛሉ።

በምርጫው የማይሳተፉ ወይም መሳተፍ የለብንም የሚሉ ሃይሎችና ሀገር ወዳድ ግለሰቦች ወያኔን ከማውገዝ ያለፈና የስርአት ለውጥ፣ ያሀገር አድን፣ የኢትዮጵያን አንድነት የማስከበር ጉዳይና ትግል ነው። ለዚህኛው ጎራ ጥያቄው መሰረታዊና በሁለት የአስተሳሰብ ፍልስፍናዎች መካከል ያለ ግብግብ ነው ብሎ ያምናል። ይህም በዴሞክራሲ ስም ተነስተው ጠባብ ብሄርተኝነትን በሚገፉና በኢትዮጵያዊነት-የሀገር አንድነትና ዴሞክራሲ መካከል ያለ ትግል ነው።
በኢትዮጵያዊነቱ ፀንቶ ከወያኔ ይሁን ወይንም ከመሰሎቻቸው ጋር በኢትዮጲያዊነት ላይ ምንም አይነት ድርድር (compromise) አይቀበሉምና አመለካከታቸው የጠራ ነው። የጠባብ ብሄርተኛነት ፍልስፍና ለአንዴም ለሁልጊዜም መመታት አለበትና።

በምርጫው የሚሳተፉት ድርጅቶችና በዙሪያቸው ያሰለፏቸው ደጋፊዎቻቸው የተለያየ አሰተያየትና አቀራረብ የያዙ፣ በአደረጃጀታቸውም ልዩ ቀርፅ ያላቸው ይመስላሉ። ሆኖም ግን ሁሉም የተለየን ነን ይበሉ እንጅ ከልዩነታቸው አንድነታቸው በጣም የላቀና እንዲያውም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ከስም ለውጥ ያለፈ አይደለም። የዚህ ብሄር ድርጅት የዚያ ብሄር ግንባር …ወዘተ ልዩነት አይደለምና። ከዚህ ምርጫ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነን በሚሉት ውስጥም ከጠባብ ብሄርተኝነት ጋር በመደራደር የብልጦችና የሞኞች ጨዋታ አስመስለው ኢትዮጵያዊነትን ከጠባብ ብሄርተኝነት ጋር ሲበርዙት እናያለን። በተወሰነ ወቅት ጠባብ ብሄርተኝነት የትግል ፍልስፍና መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን ሲወጉ የነበሩ ያው የብሄርተኛ ድርጅታቸውን ታቅፈው ኢትዮጵያዊነትን የሚሰብኩበት ወቅት ነው።ለምን ይህ ሆነ? ዞር ብለን ስንመለከት እነዚህ ተናጠል ብሄርተኞች በአሁኑ ወቅት በአንድ ጥላ ስር በመሰባሰብ የወያኔን ስርአት እንቃወማለን ይህን አንቀፅ አንቀበልም ያንን አንቀፅ እናወግዛለን እያሉ ተመልሰው ከኔ መንደር ዉጣ በኔ መንደር እኔ ብቻ በማለት ሲያስፈራሩ ይሰማሉ፣ ለምን? ከምርጫው አንደርስም ኢትዮጵያዊነት ምሳሪያችን ነው የሚሉም ወያኔን በመሳሪያ ከሚፋታተኑ ጠባብ ብሄርተኞች ጀርባ ተንጠልጥለው የወያኔን ጠባብነት እያወገዙ የኦረሞንና የሶማሌን ጠባብነት አጋር አርገው ኢትዮጵያዊነትን የበላይነት እነገፋል ይላሉ። እንዴት ሆኖ? እንዲህ አይነት አስተሳሰብስ ከምን የመነጨ ነው? ቦግ እልም እያሉ በየወቅቱ ብቅ እያሉ መነሻና መድርሻ ሳይኖራቸው፣ የተለያየ ርእስ በመያዝ በተለይም እንደአሁኑ ባለ የፖለቲካ ወቅት አትርሱኝ የሚሉ ምሁራን የአገርን ጉዳይ እንደ ሽማግሌም እንደተመራማሪም፣ እንደ ሀገር ወዳድም ያረጋቸውና ግን እናንተ ነፃነት ፈላጊዎችና ድርጅቶች እናስማማችሁ ሲሉ ይሰማሉ። ለምን የቁዋሚ ተመልካች ሚና መርጡ? እንደ ውጭ ሰውስ ለምን ሽምጋይ አሰታራቂ መሆንን ይመርጣሉ? የማይታረቁ አስተሳሰቦችን ለምን ለማስማማት ይሞክራሉ?

ጠባብ ብሄርተኝነት በህዝባችን በይፋ ከተመታና ከተቸነፈ ወዲህ ወያኔ ተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ተግራይ የህዝባችንና የአለምን አስተያየት ጥሶ በጉልበት ኢትዮጵያዊነትን ረግጦ በሚገዛበት ባሁኑ የምርጫ ወቅት፣ ከ97ቱ ምርጫ ወያኔ ተምህርት ወስዶ ምርጫው እሱ እንደሚፈልገው ሲያደርግ፣ ተቃዎሚ ነን የሚሉትም ከላይ በዘረዘርናቸው ሁኔታ ወያኔን እንቃወማለን ይበሉ እንጅ በአሁኑ የምርጫ ሂደት “ጠባብ ብሄረተኝነትን ለማዳን” “ኢትዮጵያዊነትን መልበስ” ከኔ በላይ ኢትዮጵያዊ ብሎ መለፈፍ ዋና ታክቲክ ሆኗል። ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነን ባዮችም የዚሁ ሰለባ በመሆን አብረው ይህነን ውዝንብር ያሰተጋባሉ ባጭርም በረዥምም የትግሉ ሂደት ላይ ጉዳት አሰከትሏል።

በቀጥታ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ዛሬ ወያኔ ተጠያቂ ቢሆንም በጥልቀትና በስፋት ከንደፊ ሀሳብ አንፃር ማየት ያለብን ጠባብ ብሄርተኝነት ዎነኛው ጠላታችን መሆኑን ነው። የአማራም ይሁን የኦሮሞ የጉራጌ..ወዘተ ልዩነት የለዉም።

ይህ ከሆነ ዘንዳ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን እየተዋጋ ያለው በመግዛት ላይ ያለው ወያኔ በቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ነን ባዮች በኢትዮጵያዊነት ስም ጠባብነትን እየተከላከሉ ኢትዮጵያዊነትን እያኮላሹና እየበረዙ ናችው። ይህ ከማህል ላይ አለሁ የሚል በራዣ ሃይል በጥብቅ ሊጋለጥና ልንዋጋዉ ይገባል። ስለ ስየ፡ ገብሩ; መራራ፡ በየነ፡ ሻውል፡ ብርሃኑ…ወዘተ እያሉ በተናጠል ማንሳት መጣሉ ዋጋ የለዉም። ዋጋ የሚኖርው ይህ በተለያየ መልክ ዙሪያችንን ከቦ የኛን አስተሳሰብ አምርሮ የሚዋጋውን ሃይል አጠቃላይ ጠባይና ጉዞ መመርምር የጊዜው ወቅታዊ ሀላፊነት ነው። ወቅቱን መናግር ባንችልም፡ በአንድ በተወሰነ ወቅት ይህ ሃይል ከዋናዉ ጠላት ጋር ተሰልፎ በቀጥታ ሊወጋን እንደሚችል ማመን ይኖርብናል። ከዚያ በፊት አሰተሰቡን ማጋለጥና መምታት፡ በግብዝነተ የተቀላቀሉትን ማሰረዳትና ከነዚህ  ሃይሎች እንዲነጠሉ ማድርግ ተግባራችን መሆኑ መረሳት የለበትም። ይህን ሁኔታ በአንክሮ ካላየነውና ከአሁኑ ካልተርዳነው አደጋዉ ከፍተኛ እየሆነ ይመጣል። ኢትዮጵያዊነትን የምንገፋ እንዳንደራጅና በኛ አስተሳሰብ ዙሪያ ህዝብ እንዳይሰባሰብ አሁን ወጥረው የያዙን እነዚሁ ሃይሎች መሆናችዉን አጥብቆ መረዳትና መስራት አለብን።